UW Medicine

# ውስን የሰውነት ክፍልን ማደንዘዝ

*ከቀዶ ጥገናው በፊት በተወሰነ አካባቢ ያሉ ነርቮችን ማገድ*

*ይህ ጽሑፍ ከቀዶ ጥገና በፊት ሊሰጥዎ የሚችለውን ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመን ያብራራል። ምን እንደሚጠበቅ፣ ስለ ጥቅሞቹ እና ስጋቶቹ እንዲሁም ስለተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ይናገራል።*

## ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመን ምንድን ነው?

*ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመን* የማደንዘዣ መድኃኒቶችን ይጠቀማል። ሕመም እንዳይሰማዎት ለመከላከል ከቀዶ ጥገናዎ በፊት ይሰጥዎታል። ቀዶ ጥገና በሚያደርጉበት የሰውነት ክፍል አካባቢ የማደንዘዣ ባለሙያ የሆነ ስፔሻሊስት ሐኪም ማደንዘዣውን ይወጋዎታል።

*በተወሰነ አካባቢ ያሉ ነርቮችን ማገድ* ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ የሰመመን አይነት ነው። በተጨማሪም *ውስን የሰውነት ክፍል እገዳ* ወይም *የነርቭ እገዳ* ተብሎ ይጠራል። እነዚህ (የነርቭ) እገዳዎች ብዙውን ጊዜ በትከሻ፣ ክንድ፣ እጅ፣ እግር ወይም መጫሚያ ላይ ቀዶ ጥገና ከመደረጉ በፊት ይሰጣሉ። የጥርስ ሕክምና ከመደረጉ በፊት የሚሰጠውም ተመሳሳይ ማደንዘዣ ነው።

## በቀዶ ጥገና ወቅት እነቃለሁ?



*የማደንዘዣ ባለሙያዎች ቡድን አባል ውስን የነርቭ ክፍልን ለማገድ ማደንዘዣ ሲሰጡ።*

በቀዶ ጥገናዎ ወቅት የመንቃት ምርጫ ሊኖርዎት ይችላል። ለመንቃት ከመረጡ፣ ዘና ለማለት የሚረዳዎትን የማስታገሻ መድኃኒት ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ *ነቅቶ የሚፈጸም ሕመም ማስታገሻ* (ማደንዘዣ) ይባላል።

ትክክለኛ ስለሆነው የማደንዘዣ አይነት የማደንዘዣ ባለሙያው ያናግሩዎታል። የሚከተለው ካለዎት፡

- **አነስተኛ ማስታገሻ**፣ ዘና ያደርግዎታል፤ ነገር ግን ጥያቄዎችን መመለስ እና በቀዶ ጥገና ወቅት መመሪያዎችን ለመከተል ይችላሉ።
- **መካከለኛ ማስታገሻ**፣ ቀዶ ጥገናው በሚሰራበት ወቅት እንቅልፍ እንቅልፍ ይልዎታል። በአብዛኛው ሂደት ውስጥ ይተኛሉ። ነገር ግን፣ የቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ከእርስዎ ጋር ለመነጋገር ሊቀሰቅሱዎት ይችላሉ። በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ መሆንዎን ሊያስታውሱም ወይም ላያስታውሱም ይችላሉ።
- **ብዙ ማስታገሻ**፣ በቀዶ ጥገናው ሂደት ውስጥ ይተኛሉ። በቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ መሆንዎን በትንሹ ወይም ደግሞ ምንም ላያስታውሱ ይችላሉ። ትንፋሽዎ ሊቀንስ ይችላል። መድኃኒቱ እስኪያልቅ ድረስ ተኝተው ሊቆዩ ይችላሉ።


Patient Care Services
1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195

## በቀዶ ሕክምና ወቅት ሌላ መድሃኒት እወስዳለሁ?

ሁለቱንም የተወሰነ አካባቢን የሚያደነዝዘውን ማደንዘዣ እና አጠቃላይ ማደንዘዣ ሊያገኙ ይችላሉ። አጠቃላይ ማደንዘዣ መላውን ሰውነት ይነካል። ብዙ ጊዜ፣ በክንድዎ ውስጥ ባለው የደም ሥር (IV) መስመር በኩል ይሰጣል። የተወሰነ አካባቢን የሚያደነዝዘውን ሰመመን የተሰጠበት ዋናው ምክንያት ከቀዶ ጥገና በኋላ ሕመምን ለመቆጣጠር ከሆነ አጠቃላይ ማደንዘዣ ሊሰጥ ይችላል። አጠቃላይ ማደንዘዣ ከተቀበሉ በቀዶ ጥገና ወቅት ይተኛሉ።

ሁለቱም ዓይነት ማደንዘዣዎች ከተሰጡዎት፣ የማደንዘዣ ሐኪምዎ ያነሰ አጠቃላይ ማደንዘዣ መጠቀም ይችሉ ይሆናል። ይህም የማገገምዎን ሁደት ለማፋጠን ይረዳል።

## ውስን የሰውነት ክፍልን የማደንዘዝ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

ከአጠቃላይ ማደንዘዣ ጋር ሲነጻጸር፣ አብዛኛዎቹ የተወሰነ የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመን የተቀበሉ ታካሚዎች፡-

- የማቅለሽለሽ ስሜታቸው ይቀንሳል
- በፍጥነት ይነቃሉ
- ግራ የመጋባት ስሜታቸው ይቀንሳል

## ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመንን የተመለከቱ ስጋቶች ምንድን ናቸው?

ሁሉም መድኃኒቶች እና የሕክምና ሂደቶች ስጋቶችን አሏቸው። አንዳንድ ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዙ ሰመመኖች የተመለከቱ ስጋቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ማደንዘዣው አለመስራት፣ ተጨማሪ ማደንዘዣ ያስፈልግዎታል።
- መርፌ በተወጋበት ቦታ ላይ መበለዝ ወይም ደም መፍሰስ
- ለጥቂት ቀናት የሚቆይ የመደንዘዝ ወይም ውርር የማረግ ስሜት
- ኢንፌክሽን
- የነርቭ ጉዳት

በቀዶ ጥገና ወቅት፣ የእርስዎን ዋና ዋና የጤና ጠቋሚ ምልክቶች በቅርበት እንከታተላለን። ለማንኛውም ለውጦች የልብ ምትዎን፣ የደም ግፊትዎን እና የኦክስጂን መጠንዎን እንከታተላለን።

## ማደንዘዣ መውሰድ ምን የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉት?

ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዙ ሰመመኖች እና አጠቃላይ ማደንዘዣ በሚወስዱ ታካሚዎች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ የተለመዱ፣ አልፎ አልፎ እና በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች ዝርዝር ለማግኘት ገጽ 3ን ይመልከቱ። ስለነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ከማደንዘዣ ባለሙያዎ ጋር ይነጋገሩ።



## *ከቀዶ ጥገና በፊት የሚጠየቁ ጥያቄዎች*

*የማደንዘዣ ሐኪምዎን መጠየቅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ጥያቄ ለመጻፍ ይህንን ቦታ ይጠቀሙ።*

## የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች

እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከ 100 ታካሚዎች ውስጥ ከ 1 እስከ 10 ውስጥ ይከሰታሉ።

| **የጎንዮሽ ጉዳቶች** | **ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዙ ሰመመኖች** | **አጠቃላይ ማደንዘዣ** |
|---|---|---|
| የሕመም ስሜት እና ማስታወክ | | X |
| የጉሮሮ መቁሰል | | X |
| ማዞር፣ ብዥ ያለ እይታ | X | X |
| ራስ ምታት | | X |
| ማሳከክ | | X |
| ሕመሞች፣ የጀርባ ሕመሞች | X | X |
| መበለዝ እና መርፌ የተወጋበት ቦታ ማመም | X | X |
| ግራ መጋባት፣ የማስታወስ ችግሮች | | X |

## አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች

እነዚህ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከ 1,000 ታካሚዎች ውስጥ በ 1 ውስጥ ይከሰታሉ።

| **የጎንዮሽ ጉዳቶች** | **ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዙ ሰመመኖች** | **አጠቃላይ ማደንዘዣ** |
|---|---|---|
| የደረት ኢንፌክሽን | | X |
| የጡንቻ ህመም | | X |
| የመተንፈስ ችግር (በቀዶ ጥገና ወቅት ወይም በኋላ) | X | X |
| በጥርሶች፣ በከንፈሮች እና በምላስ ላይ የሚደርስ ጉዳት | | X |
| አሁን ያለው የጤና ሁኔታ እየተባባሰ መሄድ | X | X |
| በቀዶ ጥገና ወቅት መንቃት | | X |

## በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶች

እነዚህ ችግሮች በጣም ጥቂት ናቸው። ከ 1,000 ታካሚዎች እስከ 1 ሰው ወይም ከ 100,000 ታካሚዎች ውስጥ እስከ 1 ሰው ባሉት ውስጥ ይከሰታሉ።

| **የጎንዮሽ ጉዳቶች** | **ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዙ ሰመመኖች** | **አጠቃላይ ማደንዘዣ** |
|---|---|---|
| የዓይን ጉዳት | | X |
| ከባድ አለርጂ | X | X |
| የነርቭ ጉዳት | X | X |
| የመሳሪያ ብልሽት | X | X |
| ሞት | X | X |

## ውስን የሰውነት ክፍልን የሚያደነዝዝ ሰመመንን ስቀበል ምን መጠበቅ እችላለሁ?

- በመጀመሪያ የአልትራሳውንድ ስካን ይኖረዎታል። አልትራሳውንድ የሰውነትን የውስጥ ክፍል ለማሳየት የድምፅ ሞገዶችን ይጠቀማል። ይህ ስካን የማደንዘዣ ሐኪምዎ የማደንዘዣውን መድኃኒት ለመወጋት የተሻለውን ቦታ ለማየት ያስችለዋል።
- ብዙ ጊዜ፣ ታካሚዎች አንድ የመድሃኒት መርፌ ብቻ ያስፈልጋቸዋል።
- አብዛኛዎቹ ታካሚዎች ከቀዶ ጥገና በኋላ ከ 4 እስከ 24 ሰዓታት ያህል ሕመሙ ይታገስላቸዋል። ይህ የሚወሰነው ጥቅም ላይ በሚውለው መድኃኒት ላይ ነው። (ይህን በተመለከተ) ምን እንደሚጠበቅ የማደንዘዣ ባለሙያዎ ከእርስዎ ጋር ይነጋገራሉ።

## ከቀዶ ጥገና በኋላ ስለ ሕመም ማስታገሻስ?

ከቀዶ ጥገና በኋላ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕመም ማስታገሻ በሚያስፈልግበት ጊዜ የነርቭ ማገጃ ካቴተር (ትንሽ ቱቦ) ማስቀመጥ ይቻላል። ይህ ቱቦ ቀጣይነት ያለው የነርቭ መድኃኒት ወደ ተፈለገው የነርቭ ቡድን እንድንልክ ያስችለናል።

ብዙ ጊዜ የነርቭ ማገጃ ካቴተሮች ከኦፒዮይድ ሕመም ማስታገሻ መድሃኒቶች በተሻለ ይሰራሉ። በተሻለ ሕመምን መቆጣጠር ያስጭላሉ እና በፍጥነት ለማገገም ይረዳሉ።

ካቴተር ካለዎት የኛ የአጣዳፊ ሕመም አስተዳደር (Acute Pain Management Team) ቡድን የእርስዎን ካቴተር እና ሌሎች የሕመም ማስታገሻ መድኃኒቶችን ይቆጣጠራል። ይህ ቡድን በሆስፒታል ውስጥ እያሉ በየቀኑ ይጎበኝዎታል።

## ከቀዶ ጥገና በኋላ ምን መጠበቅ እችላለሁ?

- የነርቭ ማገጃ መድኃኒቱ እስኪያልቅ ድረስ ክንድዎን ወይም እግርዎን ማንቀሳቀስ አይችሉም። የሕመም ምልክቶችን ወደ አንጎልዎ የሚልኩት ነርቮች ራሳቸው፣ ጡንቻዎችዎ እንዲንቀሳቀሱ ምልክቱን ይልካሉ።
- በማንኛውም ጊዜ ቀንም ሆነ ማታ የነርቭ ማገጃው ስራውን ሊያቆም ይችላል። ስራውን እያቆመ ሲሄድ ከባድ ሕመም እንዳይኖር፣ ሌሎች የሕመም ማስታገሻ መድኃኒቶችን በታዘዘው መሰረት መውሰድዎን ይቀጥሉ።
- ወደ ቤትዎ ሲመለሱ፣ እጅዎ ወይም እግርዎ ገና እንደነዘዙ ሊሆኑ እና ሊከብዱ ይችላሉ። ሕመም ሊሰማዎት ስለማይችል:

  - እጅና እግርን ከሙቀት ወይም ከቀዝቃዛ ቦታዎች ለመጠበቅ የበለጠ ጥንቃቄ ያድርጉ።

  - በደነዘዘ አካልዎ ላይ ጫና አይጨምሩ።

  - እግርዎ የተደነዘዘ ከሆነ እንዳይወድቁ የበለጠ ጥንቃቄ ያድርጉ። ካስፈለገ ደግፎ የሚይዝልዎት ማሰሪያ (sling) ወይም ብሬስ (brace) ልንሰጥዎ እንችላለን።

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎችዎ አስፈላጊ ናቸው። ስለነርቭ ማቆም ጥያቄዎች ካለዎት ሐኪምዎን ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።

- ❑ **የሃርቨርቪው ሪጅናል አንስቴዢያ ሰርቪስ:** በስራ ቀናት ከጠዋቱ 8 ሰዓት እስከ ቀኑ 5 ሰዓት በ **206.999.0992** ላይ ይደውሉ። ለአስቸኳይ እንክብካቤ **ብቻ** ከሰዓታት በኋላ እና በሳምንቱ መጨረሻ እና በበዓላት ቀናት ብቻ ወደ 206.520.5000 ይደውሉ።
- ❑ **ዩ ደብሊው ሜዲካል ሴንተር - ሞንትሌክ ሪጅናል አንስቴዢያ ሰርቪስ:** በስራ ቀናት ከጥዋቱ 8:00 እስከ ቀኑ 4:00 ሰዓት በ**206.598.0540** ላይ ይደውሉ።

© UW Medicine
Published PFES: 2020
Clinician Review: 05/2020
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

UW Medicine

# Regional Anesthesia

*Peripheral nerve block before surgery*

*This handout explains regional anesthesia, which you may receive before surgery. It tells what to expect, benefits and risks, and common side effects.*

## What is regional anesthesia?

*Regional anesthesia* uses numbing medicine. It is given before surgery to keep you from feeling pain. A special doctor called an *anesthesiologist* will inject the medicine into the area where you are having surgery.

A *peripheral nerve block* is a type of regional anesthesia. It is also called a *regional block* or *nerve block*. These blocks are often given before surgery on a shoulder, arm, hand, leg, or foot. It is the same type of anesthesia that is given before having dental work.

## Will I be awake during surgery?

You may have the choice to be awake during your surgery. If you choose to be awake, you may receive a *sedative* medicine to help you stay relaxed. This is called *conscious sedation*.



*A member of our Anesthesia team giving a patient a nerve block.*

Your anesthesiologist will talk with you about the right sedation for you. If you have:

- **Minimal sedation**, you will be relaxed, but able to answer questions and follow instructions during surgery.
- **Moderate sedation**, you will feel drowsy during the procedure. You may sleep through much of it. But, your surgeon can wake you up to talk with you. You may or may not remember being in the operating room.
- **Deep sedation**, you will sleep through the procedure. You will have little or no memory of being in the procedure room. Your breathing can slow. You may stay asleep until the medicine wears off.

## Will I receive any other medicines during surgery?

You may receive both regional and *general* anesthesia. General anesthesia affects the whole body. Most times, it is given through an *intravenous* (IV) line in your arm. It may be given if the main reason for regional anesthesia is to control pain after surgery. If you receive general anesthesia, you will be asleep during surgery.

If you have both types of anesthesia, your anesthesiologist may be able to use less general anesthesia. This might help speed your recovery.

## What are the benefits of regional blocks?

Compared to general anesthesia, most patients with regional blocks:

- Have less nausea
- Wake up faster
- Feel less groggy

## What are the risks of regional anesthesia?

All medicines and medical procedure involve risks. Some of the risks of regional anesthesia are:

- The block does not work, needing an extra injection
- Bruising or bleeding at the injection site
- Numbness or tingling that lasts a few days
- Infection
- Nerve damage

During surgery, we will closely watch your vital signs. We will monitor your heart rate, blood pressure, and oxygen level for any changes.

## What are the side effects of getting anesthesia?

See page 3 for a list of common, rare, and very rare side effects that can occur in patients who receive regional and general anesthesia. Talk with your anesthesiologist if you have any questions about these side effects.

## *Questions to Ask Before Surgery*

*Use this space to write down any questions you want to ask your anesthesiologist.*

## Common Side Effects

These side effects occur in 1 to 10 out of 100 patients.

| Side Effect | Regional Anesthesia | General Anesthesia |
|---|---|---|
| Feeling sick and vomiting | | X |
| Sore throat | | X |
| Dizziness, blurred vision | X | X |
| Headache | | X |
| Itching | | X |
| Aches, pains, backaches | X | X |
| Bruising and soreness from the injection | X | X |
| Confusion, memory problems | | X |

## Rare Side Effects

These side effects occur in 1 out of 1,000 patients.

| Side Effect | Regional Anesthesia | General Anesthesia |
|---|---|---|
| Chest infection | | X |
| Muscle pains | | X |
| Breathing problems (during or after surgery) | X | X |
| Damage to teeth, lips, and tongue | | X |
| Existing health condition gets worse | X | X |
| Waking up during surgery | | X |

## Very Rare Problems

These problems are very rare. They occur in 1 out of 1,000 to 1 out of 100,000 patients.

| Side Effect | Regional Anesthesia | General Anesthesia |
|---|---|---|
| Eye damage | | X |
| Serious allergy | X | X |
| Nerve damage | X | X |
| Equipment failure | X | X |
| Death | X | X |

## What can I expect when I receive regional anesthesia?

- First, you will have an *ultrasound* scan. Ultrasound uses sound waves to show the inside of the body. This scan lets your anesthesiologist see the best place to inject the numbing medicine.
- Most times, patients need only 1 injection of the medicine.
- Most patients have 4 to 24 hours of pain relief after surgery. This depends on the medicine that is used. Your anesthesiologist will talk with you about what to expect.

## What about pain relief after surgery?

When longer-term pain relief is needed after surgery, a *nerve block catheter* (small tube) can be placed. This tube allows us to send an ongoing (*continuous*) flow of nerve block medicine to a specific group of nerves.

Most times, nerve block catheters work better than *opioid* pain medicines. They give better pain control and help with faster recovery.

If you have a catheter, our Acute Pain Management Team will manage your catheter and other pain medicines. This team will visit you every day while you are in the hospital.

## What can I expect after surgery?

- You may not be able to move your arm or leg until the nerve block wears off. The same nerves that send pain signals to your brain also send the signal to make your muscles move.
- The nerve block may wear off at any time of the day or night. To avoid having severe pain as it wears off, keep taking your other pain medicines as prescribed.
- When you get home, your arm or leg may still be numb and feel heavy. Because you cannot feel pain:
  - Take extra care to protect the limb from hot or cold surfaces.
  - Do not put pressure on your numb limb.
  - If your leg was numbed, take extra care so that you do not fall. We may give you a sling or brace, if needed.

## Questions?

Your questions are important. Call your doctor or healthcare provider if you have questions about your nerve block.

- ❑ **Harborview Regional Anesthesia Service:** Call **206.999.0992** weekdays from 8 a.m. to 5 p.m. For urgent care **only** after hours and on weekends and holidays, call 206.520.5000**.**
- ❑ **UW Medical Center - Montlake Regional Anesthesia Service:** Call **206.598.0540** weekdays from 8 a.m. to 4 p.m.

© UW Medicine
Published PFES: 2020
Clinician Review: 05/2020
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu